# የተመረጡ ፍርዶች

የሰ/መ/ቁ.84623

ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች** ፡- 1. ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

2. አቶ ጌታሁን አስፋው ጠበቃ ገ/እግዛብሔር ሙናቸው ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ

**መዝገብ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልጀካቶች የደቡብ ብሄር ብሀረሰቦችና ህዝቦች ክልል የህዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታርምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩታክስ አለመክፈልን የሚመለከት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቶች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ በስር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛው አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/እና በአዋጅ ቁጥር 255/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2 አንቀጽ 56/1/2/ እና አንቀጽ 49 የተደነገገው በመተላለፍ የታክስ ከፍይነት መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመያ ቁጥር ተስጥቶት እያለ ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም እስክ ሰኔ 2001 ዓ.ም በሚያከናውነው

የንግድ እንቅስቃሴ ሽያጭ በየወሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰበሰብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማሳውቅና መክፈል ሲገባው የንግድ ማህበሩ የማስታወቅ ግዴታውን ብቻ በመወጣት የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ በሶስተኛ ወገን በተሰጠ ጥቆማ መነሻ በተደረገው ማጣራት መክፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስና አስተዳደራዊ መቀጫ ብር 9,065,777.59 /ዘጠኝ ሚሊዮን ስልሳ አምስት ሺሰባት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ያልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ነው፡፡

2. የአንደኛ ተካሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ የሆነው ሁለተኛው ተካሳሽ/ሁለተኛ ተጠሪ/ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2/ አንቀጽ 56/1/2 እና አንቀጽ 49 የተደነገገውን በመተላለፍ አንደኛው ተከሳሽ/አንደኛ አመልካች/ የአክስዩን ባለድርሻና ባለንብረት እንዲሁም በመመስራቻ ጽሁፍ የተሾመ ስራ አስኪያጅ ሆኖ እያለ ከላይ መጠኑ የተገለጸውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመክፈል ግዴታውንና ኃላፊነቱን ባለመወጣት የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት የለው ነው፡፡

3. አንደኛ ተከሳሽ በኘጅል ህግ አንቀጽ 34/1/እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3እንቀጽ 102 እና አንቀጽ 96 ተደነገገውን በመተላለፍ ከዕቃ ገዥዎች በቅድሚ ክፍያ ተቀንሶና ተሰብሰቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማስገባት የነበረበትን ብር 374,818.81 /ሶስት መቶ ሰባ አራት ሽህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም /ያልከፈለ በመሆኑ የወንጅል ክስ ቀርቦበታል፡፡

4. ሁለተኛ ተከሳሽ ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የአንደኛው ተከሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ በቅድመ

ክፍያ ቀንሶና ሰብስቦ መክፈል የሚገባውን መጠኑ በሶስተኛው ክስ የተገለጸውን ገንዘብ የልከፈለ በመሆኑ የወንጅል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት ያላቸው አራት የወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው የወንጅሉን ድርጊት አልፈጸምንም ጥፍተኛ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

5. ተጠሪ ክሱን የሚያስረዱልን ምስክሮች አሉ በማለት ሶስት ምስክሮችን በማቅረብ አስምቷል፡፡

የመጀመሪያው ምስክር አንደኛ ተከሳሽ ተጨማሪ እሴት ታክስና የደሞወዝ ግብር ገቢ በህግ አግባብ እያሰበሰበና ኤከፈለ አይደለም የሚል ጥቆማ ድርሰን፡፡ የደሞወዝ ግብር ገቢ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን እንዲያውቀው አድርገን የተጨማሪ እሴት ታክሱን በኦዲት እንዲጣራ ተደርጎ በአንደኛው የክስ ማመልከቻ መጠኑ የተጠቀሰው ተጨማሪ እሴት ታክስ አንደኛው ተከሳሽ እንዳልከፈለ ተረጋግጧል፡፡ ከዚያ በ=ላ አንደኛ ተከሳሽ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አመልከተው ጥያቄው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ሁለት ፐርስንት ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ እያደረገ ለግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ያልከፈል መሆኑንና በሶስተኛው ክስ መጠኑቴተገለጸውን ገንዘብ እንዳልከፈለ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የግብር ገንዘቡን ለማስከፈል እንቅስቃሴ ቢያደረግም አንደኛ ተከሳሽ ከዳሽን ባንክ ለወሰደው ብድር ባንኩ መደባውን በመሸጡና በባንኩ እዳ የተረፈ ገንዘብ የሌለ መሆኑ ስለተነገረን ሌሎች ንብረቶች በማፈላለግ ላይ እንገኛለን በማለት እንደመሰከሩ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡

6. ሁለተኛዋ የተጠሪ ምስክር አንደኛ ተከሳሽ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ቅጽ መሰረት በየወቅቱ ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ነገር ግን አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍሎ

አያወቅም፡፡ የድርጅቱን /አንደኛ/ ተከሳሽን ኦዲት ሠርቻለሁ፡፡ ኦዲት ስንሰራ እኛ ድርጅቱ በሳምንት አንድ ቀን ማለትም እሁድ ቀን ምርት እንደማያመርትና በወር አራት ቀናት እንደማያመርት በመቀነስ በወር ሃያ ስድስት ቀናት እንደሚያርትና በመያዝ ሂሳቡን ሰርተናል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በወር ሃያ ስድስት ቀናት የማምርት አቅሙን ተጠቅሞ የሚያመርተውን በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳቀዊያ ቅጽ አላሰወቀም የዊዝ ሆልድግ ታክሱም አለበት በማለት እንደመሰከረች ከስር ፍ/በት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

7. ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ አንደኛው ተከሳሽ የተሟላ መረጃ ይዞ አለመገኘቱንና የቀን ግምቱን መነሻ በማድረግ የግብሩን መጠን የሰሩ መሆኑን፣ የድርጅቱን ትክክለኛ የሽያጭ መጠን ለማሳወቅ የተሟላ ሪከርድ የሌለ መሆኑንና አስቸጋሪ እንደሆነ፣ ቀን ግምት በመወሰድ በወንጀል ክሱ የተገለጹት የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅደመ ተከፍይ ተቀናሽ /ዊዝሆልድግ/ታክስ የሚፈለግበት መሆኑን በመግለጽ ሪፖርት አቅርበናል የሚል ይዘት ያለው የምስክርነት ቃል እንደሰጠ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት ተረድተናል፡፡

8. አመልካቶች የመከላከያ ማስረጃ እንዲቀርቡ የስር ፍ/ቤት ብይን ስጥቶ ሁለተኛው ተጠሪ የመከላከያ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሲሆን ፣በቂ እውቀትና ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ሀይል ባለማግኘታችን የምርት ብልሽትና ብክነት ተከስቷል፡፡ ከመጋቢት 1999 እስክ 2001 መብራት ይቆራረጥ የነበረ በመሆኑ ድርጅቱ በአንድ ፈረቃ ብቻ ለማምርት ከመገደዱም በላይ ለቀናትና ለወራት ጭምር የምርት ስራ የቆመበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለዚሁም ከኢትዮጵያ ኤልክትሪክ ሀይል ኮርፓሬሽን የተጻፈልን የጽህፍ ማስረጃ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከወር ሃያ ስድስት

ቀናት በሶስት ፈረቃ እንደሚያመርት በመገመት የተሰራው የኦዲት ስራ እውነታውን የሚያሳይ አይደለም በማለት የምስክርነት ቃሉን ሰጠ ሲሆን ሌሎች የአመልክቶች ሁለት ምስክሮችም ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም በመብራት መቋረጥ ምክንያት የምርት ስራ ተቋርጧል የሚሉበትንን ሁኔታ በዝርዝር የመሰከሩ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሰዳኔ ተረድተናል፡፡

9. ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩልና በአመልካቶች በኩል የቀረቡበትን ማስረጃዎች ከመረመረ በሁላ አንደኛ ተከስ /አንደኛ አመልካች/ተጠሪ ባቀረበው በአንደኛውና በሶስተኛው ወንጅል ክሶች ውስጥ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ፤ በተጠሪ ክስ የተገለጹትን የወንጅል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፍተኛ ነው በማለት የጥፍተኝነት ውሳነተ ሰጥቷል ፡፡ ሁለተኛው ተከሳሽ /ሁለተኛ አመልካች/ ተጠሪ በሁለተኛውና በአራተኛው ወንጀል ክስ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በክሱ የተገለጹትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፍተኛ ነው በማለት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ አንደኛው አመልካች በብር አርባ ሺ ብር/ብር 40.000/ መቀጮ እንዲከፈል ሁለተኛው አመልካች ከሀምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቶች በዚገሀ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይገበኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቶችን ይገበኝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሰረት ሰርዚታል፡፡

10. አመልካቾች ጥቅምት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ክሱ የተቀሳቸው የአዋጅ ቁጥር 285/94 እና የአዋጅ ቁጥር 285/94 ድንጋጌዎች የታክሱ ስወራ ወንጀል ሚፈጸሙ ሰዎችን በወንጀል

ኃላፊ እንዲሆንና እንዲቀጡ ለማድረግ ታሰበው የታወጁ ናቸው፡፡ አመልካቶች በወቅቱ ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የማሳውቅ ግዴታችንን የምንወጣ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው ወንጀል ክስና አቅርቦ ባሰማቸው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ኦዲተሮች በወቅቱ የነበረውን በኤሌክትሪክ ሀይል እጥረትምክንያት ምርት የሚቋረጥባቸውን ጊዜዎች ሳያገናዝቡ ድርጅቱ በሶስት ፈረቃ ሃያ ስድስት ቀናት እንደሚያመርት የህሊና ግምት በመያዝ ሰሩት ሂሳብና ያቀረቡት ሪፖርት በግምት ላይ የተመሰረተና የተመረተውን እርግጠኛ ምርትና ተደረገውን ግብይት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ በዚህ ማስረጃ መነሻ የወንጅል ክስ መቅረቡም ሆነ ጥፍጠኛ ተብለን መቀጣታችን መሰረታዊ ህግ ስህተት ያለበትም ስለሆን በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በዊዝሆልዲንግ ታክስ ጥሰት ቢፈጸም እንኳኝ የወንጀል ተጠያቂነትና ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/94 ያልተደነገገ በመሆኑ አመልካቶ ያቀረበው ሶስተኛውና አራተኛው የወንጅል ክስ የህጋዊነት መርህን የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፍተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሻር እንዲያሰናብተን በማለት አመልክተዋል፡፡

11. ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካቶች አዋጅ 285/94፣ በአዋጁ ቁጥር 286/94 እና በሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/94 የተጣለባቸው የተጨማሪ እሴት ታክስና የዊዝሆልዲንግ ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቶች ማሳውቅ ግደዴታቸውን መወጣታቸው መክፈል የሚገባቸው ታክስ ባለመክፈላቸው የሚደርስባቸውን የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስቀርላቸው አይደለም፡፡ ግብር አስገቢው መ/ቤት ግብር ውሳኔ በግምት እንዲወስን የሚፈቅድለት

ህግ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ስለዚህ በግመት የተወሰነው የግብር ዉሳኔ በወንጀል ጉዳይ እንደማስረጃ መቅረቡን በመቃወም አመልካቶች ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፍተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቶች መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

12. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽህፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካቶች ላይ የሰጡትን የጥፍተኘነት ና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
13. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስና ክሱን የወንጀል መሰረታዊ ይዘት ያለው መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/96 ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የወንጅለኛ መቅጫ ህጉን በመተላለፍ የሚፈጸሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሰረተው የሚታየውና በይግባኝ የሚቀርበው በወንጅል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት እንደሆነ በአንቀጽ 48 የሚደነገግ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 94 ተመሳሳይ ይዘት ያለው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀለኛ ህግ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 111 እና 112 መሰረት የተዘጋጀን አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የህግ የሞራልና የግዙፍ ተግባር ሁኔታ በተሟላበት

ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በተለይ የህግ ጥሰት በመፈጸም ታክስ ያለመከፈል ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ የወንጀል ክስ ይዘትና ባህሪ ያለው ሊሆን ይገባዋል፡፡

14. የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎች ህግን በመጣስ ታክስን አለመክፈል ወይም በእንግሊዝው “ Tax Evasion” የሚል ርዕስ ያላቸው ሲሆን ይዘታቸው ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡የድንጋጌዎቹ ይዘት ቃል በቃል ሲነበብ ህግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሰወቀ ወ ይዘት ቃል በቃል ሲነበብ ህግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሰወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገበ ውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ስው ወንጅለው እንዲ ፈጸም ይቆጠራል በመሆኑም በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሰረት ከሚጣልበት መቀጮ በተጨማሪ ጥፍተኛ መሆኑ በፍርድ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

15. አመልክቶች ግብር የማሳውቅ ግድታቸውን የፈጸሙ መሆኑን ተጠሪ በአመልካቶች ላይ ባቀረባቸው የወንጀል ክሶች በግልጽ ያሰፈረው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንድኛ አመልካቾችን ሂሳብ ለማጣራት የተመደቡት የተጠሪ ምስክሮች አመልካቾችን በየወቅቱ በሂሳብ በግብር ማሳወቂያ ቅጹችን በመሙላት ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያሳውቁ እንደ ነበር ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካቶች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሰረት ግብር የማሳውቅ ግዴታቸውን በመተለላፍ ታክስ ባለመከፈል የፈጸሙት ግዙፍ የወንጀል ተግባር የሌለ

መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስና ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. አመልካቶች በአዋጅ ቁጥር 285/96 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሰረት መንግስትን ለማጭበ በማሰብ የማይገባቸውን የታክስ ተመላሽ በመጠየቅ ግዙፍ የወንጀል ተግባር ፈጻሙ መሆናቸውን ተተሪ በአመልካቶች ላይ ያቀረባቸው የወንጀል ክሶች አይገልጽም፡፡ ተጠሪ በአመልካቶች ላይ ያቀረቧቸው ምስክሮችም አመልካቶች የማይገባቸውን የታክስ ተማላሽ በመጠየቅ መንግስትን የማጭበርበር ስራ ስለመስራታቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡

17. ተጠሪ አመልካቶች የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በመተላለፍ የወንጅል ድርጊት ፈጽመዋል በማለት ክስከ ያቀረበው አመልካቶች ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም እስክ ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ በግምት የተወነሰነባቸው ብር 9,065,577.59 ተጨማሪ እሴት ታክስ ከነመቀመጫውና ብር 374,818.81 ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በወቅቱ አልከፈሉም በማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት አመልካቶች አንደኛ አመልካች ያመረተውን የምርት መጠንና ያከናወኑትን ግብይት ከግብይቱ የሰበሰቡትን ገቢ በየወቅቱ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያቀርቡ የነበር መሆኑ በተጠሪ ክስና ማስረጃ የተገለፀና የተረጋገጠ በሆነበት ሁኔታና አመልካቶች በየወቅቱ ባቀረቡት የግብር ማሳወቂያ ቅጽ በመጀመሪያ አንደኛ ተከሳሽ ዕቃዎችን ሲያስገባ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስና አንደኛ ተከሳሽ የፋብሪካ የምርጥ ውጤቱን ሲሸጥ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናንሰው ባላንሱ ዜሮ መሆኑንና ለመንግስት የሚከፍሉት የግብር ገንዘብ የሌለ መሆኑን በየወሩ መጨረሻ ሲያሳውቁ መኖራቸው በተረጋገተበት ሁኔታ የሚከፍሉት የግብር ገንዘብ የሌለ መሆኑን በየወሩ

መጨረሻ ሲያሳወቁ መኖራቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ኦዲተሮች ሂሳቡን ኦዲት ሲያደርጉ ፍብሪካው በሙሉ አቅሙ ማለትም በሶስት ፈረቃ በወር ሃያ ስድስት ቀናት ሊያመርት ይችላል የሚለውን የህሊና ግምት በመያዝ የወስኑት ግብበር ባለመከፈላቸው በወንጅል ቀረበባቸው ክስ እና የተሰጠባቸው የጥፍተኝነት ና የቅጣት ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 162 መስፈርት የማያኳላ መሆኑን ነው፡፡

18. በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ግብር አለመከፈል የወንጀል ተግባር ተደርጎ የተደነገገው ግብር ክፍዩ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ባሳወቀና ባልከፈለው ግብርና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ግብር ከፋዩ የያዛቸውን የሂሳብ ሰነዶችና ማስረጃዎች በተለያየ ምክንያት በመጣል በግምት በወሰነው ግብር መካከል ልዩነት ሲፈተር ግብር ክፋዩን በወንጅል ለመጤቅና ለመቅጣት በማሰብ አይደለም፡፡ ይልቁንም መክፈል የሚገባውን የግብር ገንዘብ ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤትም ንብረቶችን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር ከመከፈል ኃላፊነቱ ለማምለጥ ንብረቶችን የማሻሸና የመሰወር እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ህገ ወጥ ተግባራት በመፈፀም ግብር ያልከፈለ ግብር ከፋይን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሆነ ይኸ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 53544 በቀን 11/10/02 ዓ.ም አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

19. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካቶች በየወቅቱ ግብር የመስጠት ግዴታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል፡፡ አመልካቶች በየወቅቱ ባቀረቡት የሂሳብ ሪፖርት ለመንግስት የሚከፈል ገንዘብ የሌለ መሆኑን ያሳወቁ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በወንጅል ክሱ

የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ዊዝሆልንዲንግ ታክስ ገንዝብ ከአንደኛው አመልካች የሚፈለግ መሆኑን በመወሰን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ከሰጣቸው በኃላ አመልካቶች በህጉ መሰረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በ=ላ አመልካቶች በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ተወሰነውን ግብር ያልከፈሉት የአንደኛው አመልካች ንብረት በዳሽን ባንክ ዕዳ ምክንያት በመሸጡና የባንክ ዕዳ ተከፍሎ ቀሪ ገንዘብ ባለመኖሩ መሆኑን አንደኛው የተጠሪ ምስክር በስር ፍ/ቤት ባሰመዘገበው የምስክርንት ቃል እንደተገለጸ ተረድተናል፡፡

20. ማናቸውም ሰው የፍታብሄር ዕዳ ለመከፈል ባለመቻሉ ምክንያት በወንጅል ጥፍተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጸ 11 ተደንግጓል ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎችም ከህግ መንግስቱ አንቀጽ 13/2/ እና ከላይ ከጠቀስነው ዓለም አቀፍ ድንጋጌ ጋር በማጣጣም ሁኔታ መተርጎምና ተፈጻሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53544 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ፣ አመልካቶች ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በግምት ወሰነውን የግብር ገንዘብ ለመከፈል ባለመቻላቸው ምክንያትወ በወንጀል ተጠያቂነት ጥፍተኛ ሊባሉ የሚችሉበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም በህጉ የተደነገጉት መስፈርቶች ሳይሟሉና በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የሀሳብና የግዙፍ ተግባር ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቶች ህግን በመተላለፍ ግብር ያለመከፈል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ሰጡት የጥፍተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 11768 ሰጠው ፍርድ እና ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57769 ሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/1/ ሀ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች ሰጡት የጥፍተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ጠሻረ በመሆኑ አንደኛው አመልካች ብር 40.000/ አርባ ሺ ብር/ መቀጮ ከመክፈል በነጻ ተሰናብቷል፡፡ አንደኛው አመልካች መቀጮውን ክፍሎ ከሆነ ይመለስለት፡፡
3. የበታች ፍረድ ቤቶች የሰጡት የጥፍተኝነት ና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ ሁለተኛው አመልካች ከእስር እንዲለቀቅ በክፍሉ ማረሚያ ቤት መፍቻ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 59025

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታሁ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ

አጥናፉ ደምሴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥበበ አየለ - ጠበቃ ታገል ጌታሁን ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 501/98 መሠረት በሚሰጡት ውሳኔዎች ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚገባበትን ፍርድ ቤት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ናቸው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ የመሰረቱት የክስ ይዘት ባጭሩ፡- RISING የሚለውን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብልኝ አመልክቼ ማመልከቻዬን ያላግባብ ያልተቀበለኝ ስለሆነ የንግድ ምልክቱን እንዲመዘግብልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ማየት እንደማይችል ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብን ዉድቅ አድርÒል፣ በፍሬ ጉዳዩ ላይም

ተጠሪ የንግድ መልዕክቱ እንዲመዘገብላቸው ሲል ወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አመልካች መስሪያ ቤት በፍርድ ቤት ሊከሰስ እንደሚችል አዋጅ ቁጥር 501/98 ይደነግጋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በ=ላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የአመልካች መስሪያ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17 ስር የተደነገገ ሆኖ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ደግሞ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 49 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተሰጠው የይግባኝ ስልጣን ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማንበብ መረዳት የሚቻልና በጉዳዩ ላይ በስራ ላይ የነበሩትና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎችም ሆነ ያለው አሰራር አመልካች መስሪያ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርብ የነበረ አሁንም እየቀረበ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩ ሁነው እያለ ጉዳዩን የፌራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ቀጥታ ክስ መመልከቱ ተገቢነት የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ኤቱታው ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ተቀብሎ የተጠሪን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ አስተናግዶ ፍርድ የሰጠበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 320/1995፣ 501/98 እና 25/1988 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ በጽሁፍ መልሳቸው በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁጥር 56938 በሰበር ችሎት የአመልካች የሰበር ቅሬታ

ለሰበር ችሎቱ አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱን፣ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/2 ስር ይግባኝ የሚለው ቃል መቀመጡ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ሕጉ የተቀመጠውን የይግባኝ ቃል ትርጉም በመያዝ ሳይሆን ቅሬታ በሚል ቃል መንፈስ ነው የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችን በማንሳትና በዋቢነትም አግባብነት አላቸው ያሏቸውን ሕጎችና ድንጋጌዎችን በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በመሠረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀጽ 6/1 መሠረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው የአእምሯዊ ንብረት ሕግ መሠረት ምርመራ በማካሄድ ውሳኔ የመስጠትና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 50/98 አንቀጽ 36 መሰረት በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን በማየት ፈራሽ የማድረግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልፅ ያስገነዝባሉ፡፡ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1 ድንጋጌ ሲታይም የአመልካች መስሪያ ቤት ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 49 ሲታይ ደግሞ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትን ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ

47 መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል የሚደነግግ ነው፡፡ እንግዲህ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (The right to Appeal) እንዳለው በግልፅ ከማስቀመጡ ውጪ ይግባኙ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛው እርከን ለሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ግልጽና አሻሚነት በሌለው አነጋገር አያስቀምጥም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉን መተርጎም ተገቢ ይሆናል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1 ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "ይግባኝ የማቅረብ መብት" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "The right to Appeal" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራረብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣ የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን ሕግና ለመስሪያ ቤቱ ስልጣን የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መወሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ"Black's Law Dictionary" ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተረጎም A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially, the submission of a lower court's or agency's decision to a higher court for review and possible reversal. በሚል ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ

አንድ ፍርድን ወይም ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ /ውሳኔ/ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደረግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርዓት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሐብሔር ወይም በሌሎች ህጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፀም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐብሄር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርቦ የበታች ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል፣ እንዲለዉጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ በፌዲራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ ፅ/ቤቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ሐረግ አቀራረፁና ይዘቱ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች የተቋቋመው አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ህጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ማቋቋሙ በማስፈለጉ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 320/95 በመግቢያው ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2 ደግሞ "አእምሮአዊ ንብረት" እና "ፓተንት" የሚሉትን ቃላት ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት አእምሯዊ ንብረት

ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የምስክር ወረቀትንና ኮፒ ራይትን እንደሚጨምር በአዋጁ አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ፓተንት ማለት ደግሞ የፈጠራን ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በአዋጅ ቁጥር 123/87 መሰረት በፈጠራ በአነስተኛ በኢንዱስትሪ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትራያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/2/ ስር በግልፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህ መስሪያ ቤት ከሚያስፈፅማቸው ሕጎች መካከል አንዱ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/9/ እና 15/ ድንጋጌዎች ሲታዩም በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን ስለመሆኑ በግልፅ ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያል ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ስር የይግባኝ ስልጣኑ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን ስለመሆኑ አንቀጽ 2/1፣ እና 54 ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ሲነበቡ የሚያሳዩት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሆኖ አግኝተናል፡፡ እነዚህ ሕጎች በአመልካች መስሪያ ቤት ይፈጸማሉ ተብለው ከተጠቀሱት ሕጎች መካከል ሲሆኑ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙ የሚቀርበው በግልፅ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች መስሪያ ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 320/1995 መስሪያ ቤቱን ለማቋቋም ያስፈለገበትን ሲገልፅ አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን በግልፅ ያሰፈረ ሲሆን ይህ ምክንያት አመልካች መስሪያ ቤት ተመሳሳይ አዕምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው አካል ከመሆኑ ተዳምሮ ሲታይ ፅ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ፍ/ቤቶች ይታያሉ፣ ወይም በተወሰኑት ይግባኝ በተወሰኑት ደግሞ

ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን የሚያስፈጽማቸው ህጎች አውደ ንባብ (Contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች መ/ቤት በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በህግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም፡፡ በህጉ የተዘረጋው ስርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የተጠሪ ጠበቃ በሰ/መ/ቁጥር 56938 በቀረበዉ ተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ መወሰኑ ገልፀው ይህ ጉዳይም በተመሳሳይ መልኩ ሊስተናገድ እንደሚገባው ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም ሦስቱ ዳኞች የሚሰጡት የሰበር ትዕዛዝ /ውሳኔ/ አስገዳጅነት የሌለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው አይሆንም፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 56938 የተሰጠው ትዕዛዝ ይህን ጉዳይ በተመሳሳይ መንገድ ለመወሰን የሚያስገድድ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪ ጠበቃ ክርክርን አልፈነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 6፣17፣36፣ እና 49 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ከይግባኝ ትርጉምና አመልካች መስሪያ ቤት ከተቋቋመበት አላማና አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ከአዋጅ ቁጥር 501/98 ውጭ ያሉት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ህጎች ከዘረጉት የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት አንፃር ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ላይ አመልካች መ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ስርዓት የማስከበር እንጂ በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አለመሆኑን፣ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ደግሞ

ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን የሚያስረዳ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ለማየት አይችልም ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አዋጅ ቁጥር 501/98 አመልካች መ/ቤት ሊከሰስ እንደሚችል ይደነግጋል በሚል በደፈናው ውድቅ ማድረጉና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 153240 በ134/2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 89864 በ03/10/2002 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡